# <u>*የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ*</u>

# <u>*ለመወሰን የወጣ መመሪያ*</u>

# *አስመልክቶ የቀረበ አጭር ማብራሪያ*

*2014ዓ.ም*

*አዲስአበባ*

## የማሻሻያው አስፈላጊነት

የሠራኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተሰጠው ተግባርና ሀላፊነት መካከል በሀገሪቱ እየተመዘገበ ያለውን እድገት ለማስቀጠል የሚችል የተሟላ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አስተዳደር እንዲኖር የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት ይገኝበታል በመሆኑም የቀድሞውን የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 377/1996 መሠረት አድርጎ በስራ ላይ ከነበሩ ልዩ ልዩ መመሪያዎች መካከል የሆነው እና ከ2002ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ የነበረው የሠራተኛ ቅነሳ ስለሚፈፀምበት ሥነ ስርዓት’’ የወጣ መመሪያ አዲስ ሚልክ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መውጣት ተከትሎ መመሪያውን ማከለስና አስፈላጊ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ ይህ ማሻሻያ ተዘጋጅቷል፡፡

## የረቂቅ ማሻሻያው የዝግጅት ሂደት

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀውን ረቂቅ መመሪያ የክልል እና በከተማ ማስተዳደር የሠራኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ፣ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን፣ የኢትዮጵያ አሰሪዎች ፌዴሬሽን ኮንፌደሬሽን፣ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጎ የተገኙ ግብአት በማካተት እንዲሁም የዓለም ስራ ድርጅት ስምምነትን በማዳሰስና እና የተወሰኑ ሀገራትን ልምድ በማካተት ረቂቅ መመሪያውን እንዲዳብር የተደረገ ሲሆን በሚጨረሻም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሜጅመንት ቀርቦ በተደረገ ወይይት የተሰጠውን አስተያየት ተካቶበት እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

## የረቂቅ መመሪያው ማሻሻያ የተደረገባቸው ዝርዝር አንቀፆች ይዘት

መመሪያውን ዘጠኝ አንቀፆች የያዘ ሲሆን ከአንቀፅ 1 እስከ አንቀፅ 4 ያሉት አንቀፆች አጠቃላይ ድንጋጌዎችን ማለትም የአወጪውን ባለስልጣን (የስልጣን ምንጭ)፣ የመመሪያውን ማጠሪያና የትርጉም ክፍል የያዘ ሲሆን በአንቀፅ 4 የተፈፃሚነት ወሰን በሚመለከተው ድንጋጌ በአዋጁ የቅነሳን ትርጉም በሚያስቀምጠው አንቀፅ 29 (1) ላይ የተሰጠውን ትርጉም በተሻለ ሁኔታ ለማብራራትና የነበሩበትን ክፍተቶች ሊሞላ በሚችል አግባብ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

በመመሪያው አንቀፅ 5 በአዋጁ አንቀፅ29 (3) መሠረት የሠራኞች ቅነሳ ሲደረግ ከፍተኛ የምርት ወጤት የሚያሳዩ ሠራተኞች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ስለሚገባ ሁኔታ ከአሰሪው ጋር በምክክሩ ተሳታፊ ስለሚሆኑ የሰራተኛ ተወካዮች አመራረጥ ሁኔታ ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንቀፅ 6 ምክክሩ በምን አግባብ ሊደረግ እንደሚገባው እና ከፍተኛ የአገልግሎት ወይም የምርት ወጤት ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው ቅነሳው ከመካሄዱ በፊት አስቀድሞ ሁለትና ከሁለት ጊዜ በላይ የተሰጠ የስራ አፈፃፀም ምዘና የተገኘ ከፍተኛ ወጤት እንደሆነ እና ሠራተኛው ፈርሞ የተቀበለው ወይም የሚያወቀው መሆን እንደሚገባው

ተደንጓል ይህም በዋናነት ከቅን ልቦና ዉጪ በቅነሳው መካከተት የሌለባው ሰራተኞች ተገቢ ባልሆነ የወጡት አፈፃፀም ስርአት በማካሄድ ሊደርስ የሚችልን የስራ ዋስትና ማጣትን ብሎም ሊፈጠር የሚችል የአሰራር ክፍተትን ለማስ ያስችላል ተብሎ በሙታሙ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንቀፅ 7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በአዋጁ የተቀመጡ ሁኔታዎችን ተፈፃሚነት የሚረጋገጥ ስልጣንና ሀላፊነት ያለው ከመሆኑ አንፃር አሰሪው ቅነሳወን ከማካሄዱ በፊት ስለቅነሳው አጠቃላይ መረጃዎችን እና ሂደቶችን ያሚያሳይ መግለጫ በፅሁፍ እንዲያቀርብ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን ማመልከቻው ሲደርሰው በአምስት የሥራ ቀን ወስጥ  በአዋጁ አንቀፅ 28(3) እና 29 እንዲሁም በመመሪያው ላይ ቅነሳን አስመልክቶ የተቀመጢ ምክንያቶች፣ ቅድመ ሁኔታዎች እና ስርዓቶች መሟላታቸወን ምርመራ አድርጎ ያልተሟላ ሆኖ ካገኘው ያልተሟሉትን ሂደቶች በመጥቀስ በፅሁፍ አስተያየቱን እንደሚሰጥ ተደንግጓል፤፤ ይኸም በተለይ ህጉ የቅነሳ አፈፃፀም እንዲኖር ካስፈለገበት አላማ አንዱ የቅነሳ ወጤቱ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ ሰራተኞችን የሥራ ዉል ማቋረጥን የሚያስከት ከመሆኑ አንፃር በትክክልም በህጉ ቅነሳው እንዲመለከታቸው የተወሰኑ ሰራተኞችን ብቻ ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ከማድረግ አንፃር በህጉ የተቀመጡት ስርዓቶች ሚፈፀም በሚኒስቴሩ/አግባብ ባለው ባለሥልጣን በኩል እንዲታይ መደረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም በመመሪያው አንቀፅ 8-9 ባሉት ድንጋጌዎች ለመመሪያው አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ፣ መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ፣ የቀድሞው መመሪያ መሻሩን እና የተሻሻለው መመሪያ ስለሚፀናበት ጊዜ እንዲካተት ተደርጓል፡፡